# ዕድሜያቸው ለትምህርት ቤት ለደረሱ ፕሮግራሞች ቃለ መጠይቅ ማቅረብ

ለቤተሰብዎ ጥሩ ሊስማማ የሚችል የመዋለ ሕጻናት ማዕከል ካገኙ የሚቀጥለው እርምጃ ለጉብኝት መዘጋጀት ነው። ልጆች በማይመጡበት ወይም በማይሄዱበት ጊዜ የቃለ መጠይቁን ቀጠሮ ማድረጉ በጣም የተሻለ ነው፣ እናም ልጆቹና አዋቂዎቹ ግንኙነታቸው እንዴት እንደሆነ መመልከት ይችላሉ።

የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢን የማግኛው መንገድ፣ ይህ ጉዳይ ልክ ለሥራ ቃለ መጠይቅ ማድረግን ይመስላል። ለእርስዎ በተለይ ጠቃሚ በሆኑት ነጥቦች ላይ ያተኩሩ። ከቃለ መጠይቁ በፊት ለመዘጋጀት ሰዓት ይመድቡ። የሚመጣልዎትን ማንኛውንም ዓይነት ጥያቄ ወይም ሃሳብ ይጻፉ። ጥያቄዎችን ማሰብ እንዲችሉና ለጥያቄዎችዎ ምን ዓይነት መልስ እንደሚፈልጉ በማወያየት የሚረዳዎት ሌላ ሰው ያስፈልግዎት ይሆናል።

ባልንጀራዎን ወይም ሌላ የሚመለከተውን የቤተሰብ አባል ወደ ጉብኝቱ ቦታ ይዘው ሊመጡ ይችላሉ፣ ነገር ግን ልጅዎን ይዘው ላለመምጣት ይሞክሩ። በአንድ ሃሳብ ሳይዘናጉ አገልግሎት አቅራቢው ምን እንደሚሉ መስማት ያስፈልግዎታል። ከተቻለ ለልጅዎ ጥበቃውን/እንክብካቤውን ለሚያቀርበው ግለሰብ ቃለ መጠይቅ ማቅረብ ያስፈልግዎታል። ሥነ ሥርዓትን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን መጠይቅዎን ያረጋግጡ፣ እንዲሁም አገልግሎት አቅራቢው/አቅራቢዋ በፕሮግራሙ ላይ ስለ ሥራው/ዋ ምን እንደሚወድና/እንደምትወድና እንደማይወድ/እንደማትወድ ይጠይቁ። ደግሞም የልጅ/አዋቂ  ግንኙነቶችን በጥንቃቄ መመልከትዎን ያረጋግጡ።

የማዕከሉ ስም፡ ______________________________ የዲሬክተሩ ስም፡ __________________________

የቃለ መጠይቁ ቀን፡ __________________________

ይህ ፕሮግራም ሥራ ከጀመረ ስንት ጊዜ ሆኗታል?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

በፕሮግራሙ ሥር ስንት ልጆች አሁን ይገኛሉ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

በልጇ ዕድሜ ያሉ የልጆች ምድብ ቁጥር ስንት ነው? ልጆቹ ከየትኛው የትምህርት ደረጃና ትምህርት ቤት ናቸው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ልጆቹ ከእናንተ ፕሮግራም ወደ ትምህርት ቤታቸው የሚጓጓዙት  እንዴት ነው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

እርስዎና ሌሎቹ የሥራ ባልደረቦች የድንገተኛ አደጋ መርጃ፣ ሲፒአር፣ ወይም ሌላ ልዩ ስልጠና አላቸው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ርዕሰ መምህራንና ረዳት አስተማሪዎቹ ምን ዓይነት ሥልጠናና የትምህርት ደረጃ አላቸው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

እርስዎና የእርስዎ አገልግሎት አቅራቢዎች ትምህርታዊ/የመዋለ ሕጻናት የሥራ ጥናትና ስልጠና ይካፈላሉ?

በአማካዩ አስተማሪዎቹና ረዳቶቹ ከእርስዎ ጋር ምን ያህል ጊዜ ቆይተዋል? የስንት ዓመት ልምድ አላቸው?

የስቴቱን ደንብ በማክበር የምስክር ወረቀት ወይም የሥራ ፈቃድ አላችሁ? የሥራ ፈቃድዎን ማየት እችላለሁ?

መደበኛ ዘገባዎች ወይም ወቅታዊ ሁኔታን ማሳወቂያ ጊዜ ታወጣላችሁ?

ስለ ሥነ ሥርዓት ያላችሁ ፍልስፍና ምንድን ነው? ስለ የቤት ሥራስ?

ከትምህርት ቤት በፊት/በኋላ ለልጆቹ የምን ዓይነት ተግባራት ዕቅድ አላችሁ?

በጥበቃዎ ሥር ያሉ ሁለት ልጆች መካከል የሚመጣን አለመግባባት የሚፈቱት እንዴት ነው?

ስለ ልጄ አስተዳደግ፣ ባህርይ፣ ወይም ደህንነት አሳሳቢ ጉዳዮች ካለዎት ምን ያደርጋሉ?

ልዩ ፕሮግራሞችን ታቀርባላችሁ (ለምሳሌ፣ ዋና፣ ትምህርት ማስጠናት፣ ወይም የሙዚቃ ትምህርት)? ክፍያው ስንት ነው?

ለልጆቹ “እትምህርት ቤት” እና “ከትምህርት ቤት በፊት/በኋላን” እንዴት ትለያላችሁ?

ከእናንተ የተለየ ከሆነው የወላጅ እምነት/ፍልስፍና ጋር እንዴት አብራችሁ ትሠራላችሁ?

የምታስከፍሉት ስንት ነው? ክፍያው የሚከፈልበት ቀን መቼ ነው? ለሁለተኛ ወይም ለሦስተኛ ልጅ ተቀናሽ ሒሳብ አለ? መስሪያ ቤታችሁ ነው የሚከፈልው ወይስ ሌላ ቦታ?

የግማሽ ቀን፣ እንደመጣሁ ወይም በሰዓት የሆነ አገልግሎት አማራጭ አለ? ዘግይቶ ለመጣ የሚከፍል ሒሳብ አለ? ካለ ስንት ነው?

ልጄ በፕሮግራማችሁ ላልተሳተፈባቸው ቀናት መክፈል አለብኝ?

በየትኞቹ የባዕላት ቀናት ወይም የእርፍት ቀናት ላይ ፕሮግራማችሁ ዝግ ይሆናል?

ተጠባባቂ አገልግሎት አቅራቢ አላችሁ? በምን ዓይነት ሁኔታዎች ላይ በተተኪነት ያገለግላሉ?

ልጄ በፕሮግራማችሁ ላይ ከመካፈሉ/ሏ በፊት የምትፈልጉት ምንድን ነው?

በህምም ጊዜ ያላችሁ ፖሊሲ ምንድን ነው?

በፈቃድ መድሐኒት ትሰጣላችሁ?

የመለማመጃ ወይም የሙከራ ጊዜ አላችሁ?

ልጄ የሚጠቀምባቸውን ክፍሎችና መገልገያዎች ተዟዙሬ መመልከት እችላለሁ?

ቃለ መጠይቅ ለማድረግ የሦስት ቤተሰቦችን ስምና የስልክ ቁጥር ልትሰጡኝ ትችላላችሁ?

________________________________________

________________________________________

ከቃለ መጠይቁ በኋላ ከውውይቱ ጠቃሚ ክፍሎችን እንደገና ይመልከቷቸው። በቃለ መጠይቁ ጊዜ ውይይት ስለተደረገባቸው ጉዳዮች ጥሩና መጥፎ ሁኔታዎች ዝርዝር ያውጡ። ሃሳብዎን ለማሰባሰብ እንዲረዳዎት የሚሰማዎትን ለትዳር ጓደኛዎ ወይም ለሌላ ለሚመለከታቸው ሰዎች ያወያዩ። አንዴ ምርጫዎችዎን አጥርተው አንድ ወይም ሁለት አማራጮች ካወጡ በኋላ ዲሬክተሩ የሚሰጡዎትን ለእያንዳንዱ ሃሳብ ሰጪ ቤተሰብ ይደውሉ።